## ዘመነ መንደርተኛ (ቁጥር አራት)

## ድርብ አቋም ከሚገፉ አስመሳዮች እንጠንቀቅ!




**ብስራት ኢብሳ (ሆላንድ) 16/11/2020**

**አንድ ድርብ አቋም የሚያራምድ ጥላቻ የተጠናወተው አስመሳይ ከ100 ጠላት በላይ ሀገርን ይጎዳል!**

Double dealer የሚለውን የትርጉም ስፋት ለመረዳት ወደ ጉግል ቱርጁማን ክፍል ጎራ ብዬ ያገኘሁት፥ double-crosser, traitor, two timer, betrayer, beguiler, cheater, deceiver, trickster, slicker, የሚለውን በአማርኛችን ተመሳሳይ ቃላት ስፈልግ፣ አስመሳይ፣ አድርባይ፣ አታላይ፣ ቅጥረኛ፣ ባንዳ፣ ከሃዲ… ከፈረንጁ ቃላቶች በላይ ብዙ ያልጠቀስኳቸው ቅጽሎች ብቻ ሳይሆኑ፣ ድርጊቱንም በተግባር የሚያውሉ ማስታወስ ጀምሬ ስለበዙብኝ ትንሽ ሃሳቤን አካፍያችሁ ላራግፋቸው ፈለኩኝ፡፡

ስለ ትህነግ (TPLF) እና በአምሳሉ ስለፈጠራቸው እንደ ኦነግ ሸኔ … አይነት ድርጅቶች እስካሁን ድረስ በሕዝባችን ላይ እያደረሱ ያሉትን ጥፋቶችን ሳስብ፣ ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ የነሱን ተግባር የማይገልጽ ስለሌለ፣ ድርብ አቋም አራማጅ የሚለው Double dealer ሁሉንም ጠቅልሎ በተሻለ ይገልጻቸዋል፡፡

ይህ በዘር የተሰባሰበ ትህነግ የሚባል ከሃዲ ቡድን፣ በቅርቡ በሰሜኑ የሀገር መከላከያ ሰራዊታችን ውስጥ በገዛ የሙያ ባልደረቦቻቸው ላይ አድርሰው ያየነው ትልቅ ክህደትና ያስከተለውም ጥፋት ከውጭ በመጡ ጠላቶች ሳይሆን በነዚህ በሀገር በቀል ከሃዲዎች መሆኑ ሊገርመን አይገባም፡፡ ምክንያቱም በታሪካችን ትህነግ እና ክህደት ተለያይተው ስለማያቁ ደግ ነገር ከነሱ መጠበቅ አልነበረብንም፡፡

አምነዋቸው ከጎናቸው በተሰለፉ የሙያ ባልደረቦቻቸው ላይ ያደረሱት ጭፍጨፋና ከዛም በኋላ ተሰምቶ ለማመን የሚያስቸግር አሰቃቂ የጭካኔ ተግባር የተቀነባበረውና ስራ ላይ የዋለው፣ ይህ የባእዳንን ተልእኮ ለማስፈጸም በተደራጀው በትህነግና በአምሳሉ በፈጠራቸው ኦነግ ሸኔን…ወዘተ በመሳሰሉት ዘረኛ ድርጅቶች ትብብር ነው፡፡ ይህ ከሱ ውጪ ያለውን ማኅበረሰብ አምርሮ የሚጠላና ለራሱ ማኅበረሰብም ግድ የሌለው ከሃዲ አስመሳይ ቡድን፣ ይህንን የጭካኔ ተደጋጋሚ ጥፋት እያደረሰ ያለው፣ በትግራይ ሕዝብ ስም እና መሃከል ሆኖ የወያኔ አቋም የትግራይ ሕዝብ አቋም እንደሆነ ደጋግሞ እየማለ ነው፡፡

ሃይማኖቱን ባህሉንና ኢትዮጵያዊነቱን የሚወደው የትግራይን ሕዝብ፣ እንደ ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ሁሉ ይህ መሰሪ ድርጅት እሱንም በሃይል ተጭነው ከሌላው ወገናችን ጋር እያጋጩት ለራሳቸው መጠቀሚያና መደበቂያ ዋሻ እንዳደረጉት ግልጽ ነው፡፡ በዚህ ወሳኝ ትህነግን ከሕዝባችን ትከሻ ለማራገፍ እየተወሰደ ባለው ቆራጥ እርምጃ፣ የትግራይ ሕዝብም ከመከላከያ ሠራዊታችን ጎን ሆኖው እራሱንም ጭምር ከነዚህ ከሃዲ ቡድን ነጻ በማውጣቱ ተግባር ሙሉ ለሙሉ እንደሚሳተፍ ተስፋ ይደረጋል፡፡ ሆኖም የዚህ ዘረኛ ድርጅት መሸነፍ ማለት መሪዎቹን ብቻ አሳዶ ይዞ ለፍርድ ማቅረብ ሳይሆን፣ ለሠላሣ ዓመታት የሀገራችንን

ሕዝብን በቋንቋና በክልል ፌደራሊዝም ከፋፍለው እያጋጩ በስልጣን እንዲቆዩ ያደረጋቸውን “ሕገ አራዊት” ከሕገ መንግስቱ ፍቆ ከነሱ ጋር አብሮ ሲወገድ ብቻ ነው ወያኔ ተሸነፈ ማለት የሚቻለው፡፡ ችግራችን ከሰዎቹ ብቻ ሳይሆኑ እነሱ ለ30 ዓመት በመላው ሀገራችን በተሳሳተ መንገድ የቀረጹትን ትውልድ ከዘረኝነት ፈውሶ ሁሉንም ሕዝብ እኩል እንዲወድ በትክክለኛ መንገድ የማነጹ ተግባር ነው፡፡

የትህነግን (TPLF) ድርጅት የተነሱበትን መሠረታዊ ዓላማም ሆነ፣ በሂደት ያያነው የድርጅቱ ታሪክ፣ እጅግ በፍጥነት ተለዋዋጭና ፋሽስታው ባህሪ ያለው ቡድን ነው፡፡ በስልጣን ላይ አታሎ ለመቆየት በዓለም ላይ ካሉ የፖለቲካ ዘይቤዎች(Ideology)ሊያጨበረብሩበት የሚጠቅም ከመሰላቸው ያልቀነጣጠቡት የለም፡፡ “ከመደብ ትግል የብሔር ጭቆና ይቀድማል” ብለው ጀምረው “በአልባንያ ሞዴል” አቋርጠው፣ በህንፍፍሽና በቦናፓርቲዝም ውቅያኖስ ቀዝፈው “አብዮታዊ ዲሞክራሲ”እያሉ ያላምታቱት ነገር የለም፡፡

በታሪካችን ያየናቸው ሁሉም የፋሽስት ፓርቲዎችን አንድ የሚያደርጋቸው፣ ለሚቀርጹት የፖለቲካ ዘይቤ ማደናገርያቸውን የሚቀነጣጥቡት፣ ሕዝብን እያታለሉ ጨቁኖ ለመግዛት ይረዳናል ብለው ከሚያስቡት ከሁሉም አይነት የዓለም ፍላስፍናዎች ለነሱ የሚመቸውን ብቻ እየጨለፉ በመውሰድ ነው፡፡ ይህንን ሂትለር፣ ሞሶሎኒ፣ ፍራንኮ፣...ወዘተ ሁሉም የፋሺስት ድርጅት መሪዎች ተጠቅመውበታል፡፡

ይህ ሁሉ የርእዮተ ዓለም ጋጋታ ለሕዝብ እያስመሰሉ የሚያምታቱት ዋነኛው ዓላማቸው፣ የተወሰኑ የፓርቲው ቁንጮ መሪዎችና ቤተሰቦቻቸው በማንኛውም መንገድ በስልጣንና በሃብት አግዝፎ ለማቆየት እንጂ የሕዝብና የሀገርን ጥቅም ከማስጠበቅ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ ይህንን ፍላጎታቸውን ወደ ተግባር ለመቀየር ባደረጉት ረዥም የጭቆና አስተዳደር፣ የተቃወሟቸውን ገለዋል፣ ገርፈዋል፣ ያለአግባብ አስፈርደውባቸዋል፣ አስግዘዋል፣ ደብዛ አስጠፍተዋል፣ የባእዳንን ጥቅምም አስጠብቀዋል....ወዘተ፡፡

ትህነጎች በታሪካቸው ሁሌ ጥቃት ሲበዛባቸውና የሚሸነፉ ከመሰላቸው ጊዜ ለመግዛት፣ እርቅ ይጠይቃሉ፣ ገላጋይና ሽምጋይ ጭምር አማላጅ እየላኩ በማዘናጋት፣ በጎን ማነቂያ ገመድ እና መስቀያ ቦታ ያዘጋጃሉ፡፡ በተደጋጋሚ እንደ እነሱ በትግራይ ውስጥ እየተንቀሳቀሱ ደርግን ለመጣል ይታገሉ የነበሩ መሰል ድርጅቶችን አብረን እንታገል፣ እርቅ እናካሂድ እያሉ ጠርተው በጥይት ጨፍጭፈው ያጠፏቸውና፣ እንወያይ ብለው ለስብሰባ ጠርተው ሊደመስሱ የሞከሯቸው ብዙዎች ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ፣ (ግንባር ገድሊ ሃርነት ትግራይ)ግገሃት፣ ኢዲዩ፣ ኢሕአፓ፣ ሻቢያ፣ ኦነግ፣ ቅንጅት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ **በሚካሄደው ጦርነትም ትንሽ ደከም ሲሉ ጊዜ ለመግዛትና የክህደት ታሪካቸውን ለመድገም ይሞክራሉ!!**

ሰሞኑን የሰሜኑ ጦራችን ለሃያ ዓመት ቤተሰቦቻቸውን ጥለው ትግራይን ከአደጋ ለመከላከል፣ ሕዝብን እያገለገሉ ግዳጃቸውን በመፈጸም አብረዋቸው የነበሩትን የሙያ ባልደረቦቻቸውን፣ በተለመደው የወያኔ የሀገር ክህደት ተግባር የውጪ ጠላት እንኳን የማያደርገውን፣ በተኙበት ጨፍጭፈው በአሰቃቂ ሁኔታ የገደሏቸውንና ከሞቱም በኋላ ያደረጉት አሳፋሪ ተግባር የትህነግ ቋሚ ፋሺስታዊ ባህርይ ነው፡፡

ይህ በቅርቡ በወያኔ እና ኦነግ ሸኔ ጽንፍ በረገጡ አክራሪ ብሔረተኞች ትብብር፣ በተለይ በአማራው ላይ ያነጣጠረና በሌሎችም ያካባቢው ተወላጆች ባልሆኑ ወገኖቻችን ላይ በተደጋጋሚ ተከስቶ እንዳየነው አይነት ጭካኔ፣ በሙያ ባልደረቦቻቸውና በራሳቸው ዜጎች ላይ መሆኑ፣ በዓለም የክህደት ታሪክ ምናልባት የመጀመርያውን ቦታ ሊይዝ ይችል ይሆናል፡፡ ይህ ከነሱ ማኅበረሰብ ውጪ ያለውን ዘር በጠላትነት ማየትና አድፍጦ በአሰቃቂ ሁኔታ በመግደል፣ ለሞቱት ጭምር ከሰው እንዳልተፈጠሩ፣ በዱር አውሬ ላይ እንኳን ሊታሰብ የማይገባ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት፣ እንኳ ከሀገሬ ሰው ከጠላት እንኳን አይጠበቅም፡፡ በዚህ ተግባር ያላዘነና ያላለቀሰ ሀገሩን የሚወድ ኢትዮጵያዊ አለ ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ዘረኝነት የመጨረሻው ጥግ ሲደርስ ምን ያህል ጨካኝና ለሰብአዊ ፍጥረት ቅንጣት ርኅራሄ እንደሌለው፣ ከዚህ ትምህርት ወስደን በጽኑ ልንከላከለው ይገባል፡፡

የዘረኝነት በሽታ፣ አንዳንዶች እንደሚነግሩን በተወሰነ ማኅበረሰብ ውስጥ ብቻ የሚከሰት፣ የተወሰነው ማኅበረሰባችን ከዚህ ተላላፊ በሽታ ነፃ እንደሆነ አድርገው ለማሳየት የሚሞክሩት አንዳንዶች በየዋህነት

እንደሆነ ቢታወቅም፣ የወያኔን ፈለግ ተከትለው የመጡት ግን እኛ ስናደርገው ለምን ይወገዛል? የሚሉት፣ “እኛ ስናደርገው ትክክል ነው” ማለታቸው ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በዘረኞቹ ሰፈር ስለ የኢትዮጵያ አንድነት ማንሳት በሁሉም ማእዘን በቆሙ ጽንፈኞች በጠላትነት አስፈርጆ ያስጠምዳል፡፡ ኢትዮጵያዊነት ከጠነከረ የአክራሪዎችን ሰፈርን ስለሚያጠወልግ፣ አባሎቻቸው ወደ አንድነት ሰፈር እንዳያማትሩ አዳዲስ “ትርክት” እየቀመሙ ከብሔራዊ አስተሳሰብ አርቀው ወደ ጥግ ገፍተዋቸዋል፡፡ በዚህ ወያኔን ለማንበርከክ እየተካሄደ ባለው ጦርነት፣ መከላከያ ሠራዊታችን፣ የየአካባቢው ሚሊሺያና ሀገር ወዳድ አብሮ ደሙን እያፈሰሰ ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎችን መግቢያ መውጫ እያሳጣ ባለበት ሰዓት አብሮ መቆም ሲገባ፣ ከወዲሁ የክፍፍል አጀንዳቸውን በስላሽ እያስገቡ፣ የተነሳሳውን ብሔራዊ ስሜትና ሀገር ወዳድነት በዚያው እንዳይቀጥል በመስጋት ልዩነት እየፈጠሩ ለመከፋፈል ወደ የጀግና ሽሚያ፣ የታሪክ ሽሚያ፤ የምርኮ ሽሚያ፣ ባጠቃላይ ወደ አንድነት ሳይሆን ወደ የመንደራችን አንሰን እንድናስብ የሚሞክሩትን ታዝበናል፡፡ ወያኔ በሠራዊታችን ላይ ባደረሰው ጥፋት ከሁሉም ማእዘን ተቆጥቶ የተሰለፈው ሕዝብ፣ ከመከላከያ ሠራዊታችን ጎን በመሰለፍ ከባድ ዋጋ እየከፈለ የሚያስመዘግበው ድል ለዚህ ወይም ለዛ ማኅበረሰብ ሳይሆን ለኢትዮጵያኖች ነው፡፡

ትላንት የትህነግ እና የኦነግ ሸኔ... ጽንፈኞች ከደረሱበት የጥላቻና የጭካኔ ተግባር ትምህርት ወስደን የሚያስተሳስረንንና የሚያቀራርበንን በጎ ነገሮችን እንደገና እየሰበሰብን ዘረኝነትን ከሀገራችን በጊዜ ማስወገድ ካልቻልን ከፍተኛ አደጋ ላይ ነን፡፡ በተለይ በየማኅበረሰቡ በፉክክርና በመፈራራት እየደለበ ያለው የክልል ጦር ወደ ኅብረ-ብሔራዊ የሀገር መከላከያ እየተቀየጠ ካልተዋቀረና፣ “በአብዮታዊና ፌደራል ስም” ሕዝብን አንደኛ እና ሁለተኛ ዜግነት እየሰጠ በማጨራረስ አፈናቅሎ እዚህ ደረጃ ያደረሰን፣ ጨርሶ ሳያፈርሰን መወገድ አለበት፡፡ ይህ በባለሞያ ተጠንቶ፣ መላው ኢትዮጵያ የሁሉም ሕዝባችን እኩል የጋራ ሀገር መሆንዋን የሚያረጋግጥ የዘረኞችን መግቢያ ቀዳዳ በሚደፍን አስተዳደራዊ መዋቅር ካልተቀየረ የተከፈለው መስዋዕትነት ዋጋ ያጣል!፡፡

**የዘር ጥላቻ ከግል/ቡድን ጥቅምና ስልጣን ጥም ጋር በጣም የተቆራኘ ነው፡፡** እንቅስቃሴውን ሲጀምሩ ድርብ አቋም ይዘው እንደ ቡድንም ሆነ ግለሰብ ለአንድ ብሔር የሚቆረቆሩ በማስመሰል ነው፡፡ አንዱን ማኅበረሰብ ነጥሎ እስከ አንጀት መውደድና፣ ከዛ ውጭ ያሉትን አምርሮ በመጥላት በጠላትነት መፈረጅ፣ ብዙ እውቀትንና ችሎታን ስለየማይጠይቅ ባጭር ጊዜ ብዙ አባላትንና አጃቢዎችን ማሰባሰብ ያስቻላል፡፡

አባላት የመሪዎቹን የተደበቀ ምክንያት (motive) አለ ብለው ስለማይጠረጥሩ የሚነግሯቸውን በሙሉ ለመቀበል አዕምሮዋቸው ክፍት ነው፡፡ መሪዎቹ ተከታዮቻቸውን በምክንያት ሳይሆን በስሜት ቁጭት ውስጥ እንዲገቡና በበቀል እንዲረኩ የሚወስድ መንገድ ጠንቅቀው ስለሚያቁ፣ ከጥላቻ ትርክታቸው ጋር በዘፈንና በሽለላ ጭምር እየኮረኮሩ አቋም ያስይዟቸዋል፡፡ አንዴ በሚፈልጉት ደረጃ ተከታዮቻቸውን ከመረዟቸው ቦኋላ፣ እንደ ግለሰብ የማሰብ ችሎታቸው ይመክንና ከላይ መሪዎቹ የሚነገሩቸውን ብቻ ነው እንደገደል ማሚቶ የሚደግሙት እንጂ ለመወያየት የማዳመጥ ችሎታ እንኳን የላቸውም፡፡

ለዚህ ነው ጥንፍ የረገጠ ብሔረተኝነትን ገና ዳዴ ሲሉ ቶሎ ነቅቶ ያልገባቸውን እያስተማሩ ለመመለስ መሞከር እንጂ፣ አንዴ እንደ ካንሰር ካደገና በየማኅበረሰቡ ገብቶ ከተሰራጨ ቦኋላ ለማስወገድ ቀላል አይሆንም፡፡ ምናልባት ጥላቻውና ጭካኔው ድብቅ እየሆነ ቶሎ ለማየት ያስቸግር እንደሆን እንጂ፣ ማስተዋል ለሚፈልግ፣ አክራሪ ብሔረተኛነት ጭምብሉ ከመገፈፉ በፊት ገና በለጋነቱ ታዛቢን ለማደናገር፣ ዳር ዳር ሲሉ የሚሄዱባቸው ጠመዝማዛ መንገዶችና ውስብስብ አስተሳሰቦች ባጋጣሚ አይደሉም፡፡ ከእውነት መራቃቸውን ስለሚያውቁት፣ ሲቀየሩ ኩርፊያ፣ ቁጣ፣ ስድብ፣ ክስ፣ ዛቻ፣ ምክንያት ያበዛሉ፡፡

የፖለቲካ ነጋዴዎቹ በራሳቸው ስለማይተማመኑና (Insecure ) የአባላቱን እንቅስቃሴ ይቆጣጠራሉ፡፡ መሪዎቹ ምንም ነገር ከቁጥጥራቸው ውጭ እንዲወጣ ስለማይፈልጉ፣ አባላቶቻቸውን ከሴክት ባላነሰ መንገድ የየቀኑን እንቅስቃሴያቸውን መረጃ በመቀያየር ሽፋን የአባላትን የታማኝነት ደረጃ ይመዝናሉ፣ መመሪያና ማብራሪያ ያስተላልፋሉ፣ ትንሽ ገብቶት መጠየቅ ወይም ከሴክቱ የተለየ አቋም መውሰድ ከጀመረ፣ ለጊዜው ከቡድኑ በማግለል “የደከመበት ምክንያት”ተፈልጎ ምናልባት በሚያምነውና በሚቀርበው ሰው እንደገና ይጫናሉ (update)፡፡ በራሳቸው አንድ ወጥ በሆነ አመለካከት በቀረጿቸው

ተከታዮችና፣ በትናንሽ ስልጣን የሚረኩና እንደጎዳና ስልክ ሳንቲም ሲጨምሩባቸው የሚሰሩ ሁለገብና “ድንበር ዘለል” አስለቃሾችን፣ (ቀስቃሾችን) እያዘጋጁ፣ከትናንሽ ማኅበራትና የዕምናት ስፍራዎች እስከ ሀገራዊና አኅጉራዊ፣ ብሔራዊ እንቅስቃሴዎችን በተለያየ ዘዴ በመቆጣጠርና ሽባ በማድረግ፣ ለነሱ የጎጥ አደረጃጀት ዓላማ ማስፋፍያ አድርገው ለመጠቀም ሲጥሩ ይታያል፡፡

እነዚህ የራሳቸውን ጥቅም በአንድ ብሔር ስም ማጋበስ የሚፈልጉ መርህ የሌላቸው የፖለቲካ ቱጃር ነጋዴዎች፣ አክራሪ ብሔረተኝነትን እንደ ከዘራ ለመመርኮዝ የሚፈልጉበት ዋናው ምክንያት፣ በተረጋጋ ሰፊ ማኅበረ ሰብ ውስጥ ተምረውና ተወዳድረው ሊደርሱ የማይችሉበትን ስልጣንና ሃብት፣ በሚመርጡት ውስን ማኅበረሰብ ውስጥ መሪና ቱጃር ለመሆን ፉክክሩ ቀላልና አቋራጭ ስለሚመስላቸው ነው፡፡ ታዲያ ይህን ዓላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ መጀመርያ ቆመንለታል የሚሉት ሕዝብ፣ ድርጅት፣ የዋህ ተከታይና በአንፃሩ በጠላትነት የሚመደብ ሕዝብ፣ ስሜት መኮርኮርያ ትርክት....ወዘተ ያስፈልጋቸዋል፡፡

በመጀመርያ እነዚህን ክፍሎች መለየት የሚቻለው፣በሚያሳዩት ጸረ ሠላምና አንድነትን አቋማቸው ነው፥ የእርስ በርስ ግጭት ቆሞ ሠላም ከወረደ፣ የነዚህን “የፖለቲካ ነጋዴዎች” መተዳደርያ የጥቅም መስመር ስለሚዘጋ፣ ሠላም የሚመጣበትን መንገድ በሙሉ በሰለጠኑበት ተንኮል ማጨናገፍ ይችላሉ፡፡ ብሔራዊ የጋራ አጀንዳ፣ ብሔራዊ ስሜት፣ ብሔራዊ ቁጭት፣ ብሔራዊ እድገት፣ ብሔራዊ ክብር፣ ብሔራዊ ጦር፣ ብሔራዊ የሀገር ፍቅር ...ወዘተ ከውስጣቸው ነጥፏዋል፡፡ ብሔራዊ የሚለውን ስፍራን የተኩት የወጡበትን ብሔር ስም ነው፡፡ የቀውስ ነጋዴዎቹ የሀገር ፍቅር የሚለውን የተኩት፣ የስልጣን ፍቅር፣ የሃብት ፍቅር፣ የንዋይ ፍቅር በሚለው ነው፡፡ በዚህ ፍቅር ነው የሚኖሩትም፣ የሚገሉትም፣ በመጨረሻ የሚጠፉትም፡፡

አባሎቻቸው የጎጥ መሪዎቹ ከሚሰጧቸው መመሪያ ውጭ፣ ከሌሎች ጋር ተባብረው ምንም ሀገራዊም ሆነ ከባቢያዊ ጉዳዮች እንዳይሳተፉ ነቅተው የሚጠብቁ ዘበኞች ስላሏቸው ሃሳባቸውን እንኳን ለመስጠት ይፈራሉ፡፡ ወይም ተከታዮቻቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸ መሪዎቻቸው ቀደም በማለት አቅጣጫ ያሳዩዋቸዋል፡፡ ማኅበርን፣ የእምነት ቦታዎችን፣ እቁቦችን፣ ሀገራዊና አህጉራዊ እንቅስቃሴዎችን ብቻ ሳይሆን፣ቢችሉ ሁለትና ሰው ያለበትን የጓደኝነት እንቅስቃሴን መቆጣጠር (CONTROLE!) የሚፈልጉት፣ ምንም ነገር ከመሪዎቹ ፍላጎትና ቁጥጥር ውጭ እንዳይውጣ ነው፡፡ የወያኔ አንድ ለአምስት አደረጃጀት ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ ከዛ በኋላ በብሔራዊ ደረጃ ተገናኝተን በሀገራችን በደል ለሚደርስበት ሕዝብ ድምጻችንን እንድናሰማ፣ ወይም ደሙን እያፈሰሰ ካለው ብሔራዊ የመከላከያ ሠራዊታችን ጎን ተሰልፈን ድጋፍ እንዳንሰጥ ከስር ከስራችን መበተኛ ከምሱሩን እየቀበሩ መከፋፈሉን መርጠውታል፡፡

እነዚሁ በብሔር ፖለቲካ ሽፋን ከሕዝብና ከሀገር በዘረፉት ሃብትና ስልጣን የደለቡት የወያኔ ሞተር አንቀሳቃሽ ስለሆኑ፣ ድርጅታቸውም አደጋ በሚያጋጥመው ጊዜ በዋነኛነት ኪሳራ ላይ የሚወድቁት እነሱው ስለሆኑ፣ እሳቱን ለማጥፋት ቀድመው የሚፍጨረጨሩትም እነሱ ናቸው፡፡ እነዚህን ቱጃር ነጋዴዎች ኪሳቸውን ማደህየትና ዝርፊያውን ማጋለጥ የአክራሪዎችን የእስትንፋስ መስመር መቁረጥ ስለሆነ፣ ሀገር ውስጥ መንግስት እየወሰደ ያለውን፣ ጽንፈኝነትን መታገልና ማዳከም እንደሆነ ተደርጎ መወሰዱ ሊደገፍና ሊበረታታ የሚገባው እርምጃ ነው፡፡ ሆኖም እርምጃው ወደ ዘር ጠል እንዳይሄድና ጥሮ ግሮ በላቡ ያገኘውና እንዚህን በሕዝብ ደምና ዝርፊያ ከከበሩት ጋር እንዳይምታታ ጥንቃቄ ያሻል፡፡

<u>አንድን ድርጅት ወይም ግለሰብ በዘረኝነት የሚያስፈርጀው እራሱን ከጥቃት ስለተከላከለ ወይም ለልማትና ለተራድዖ ለመሳሰሉት በጎ ተግባራት ስለተቋቋመ ሳይሆን! ቆመንለታል ከሚሉት ማኅበረሰብ ውጪ “እነሱ” ብለው የፈረጇቸውን ሕዝብ ዝቅ አድርጎ ማየት፣ መጥላት፣ ማስጠላት፣ መናቅ፣ ማዳላት፣ መጠራጠር፣ መሳደብና ምክንያት እያመቻቹ ማጥቃት ሲጀምሩ ነው፡፡</u>

ነገር ግን ጽንፈኛ ብሔረተኞች፣ ጥቃቱን ከሁሉም ማኅበረሰብ ጋር ተባብሮ መመከት እየቻሉ፣ ምክንያት አገኘን ብለው፣ የራሳቸውን የዘር ጥላቻ ስሜት በአንድ ብሔር ተቆርቋሪነት ሽፋን ችግሩን ወደ ሕዝብ ውስጥ በመግፋት ለራሳቸው የተደበቀ ዓላማ ለመጠቀም ከሚፈልጉት ጋር መምታታ የለበትም፡፡ ሌሎችም አክራሪ ብሔርተኞችን ከለላ አድርገው፣ አንዳንዴ ከነሱንም የባሱ <u>እያስመሰሉ</u> ለግል

ጥቅማቸውና ለስልጣን ፍላጎታቸው እንደ መሰላል ሊጠቀሙበት ድርብ አቋም ይዘው በስላሽ የራሳቸውን ግብ ለመምታት ስለሚደባለቁት ብዙ ትኩረት ስላላገኘ፣ በተግባር ከሚታየው ተለዋዋጭ ባህሪያቸው አንዳንዶቹን ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ እነዚህን አክራሪ ብሔረተኞችን እንደ ከዘራ እየተደገፉ በስላሽ የረሳቸውን የግል አጀንዳ ስለሚያካሂዱት ድርብና ድርብርብ አቋም አራማጆችን ተጨማሪ ችግር በበቂ ትኩረት አልተሰጠውም፡፡ እስካሁን በዘልማድ የአንድነትና የብሔር ፖለቲካ አራማጆች እየተባለ ሦስተኛዎቹ በሁለቱም የማያምኑ፣ ነገር ግን ሁለቱንም ለግል ጥቅማቸው እንደአስፈላጊነቱ ተራ በተራ እንደ ሸሚዝ በመቀያየር፣ የራሳቸውን የገንዘብና የሰልጣን ፍላጎት አድፍጠው ያረካሉ፡፡

ባደባባይ ስለ ስለ ሀገር አንድነት፣ እኩልነትንና ዲሞክራሲ "እየሰበኩ" በማጀት ለተወሰነ ብሔር፣ ቋንቋና የእምነት የበላይነትን ለማምጣት ያገዙ በማስመሰል በስላሽ የራሳቸውን ጥቅም የሚያሳድዱ ድርብርብ አቋም እየያዙ ብቅ የሚሉ አስመሳዮችን ለይቶ ማወቅ ትግሉን ከማጥራቱም በላይ ሂደቱን ያፋጥናል፡፡ በነዚህ ፈርጅ ውስጥ አንዳንዴ ኢትዮጵያዊ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የአንዱን ብሔር የነጠላ ጫፍ ጨብጠው እንደ እስስት ገጽታቸውን በመቀያየር እያስመሰሉ፣ በሕይወት መኖራቸውን ለማሳየት ዕድሜያቸውን ብቻ እየቆጠሩ የሚኖሩ አስመሳይና አድርባይ የፖለቲካ ድርጅቶችንም ያጠቃልላል፡፡

በኢትዮጵያ አንድነት ሽፋን በስውር ከሚንቀሳቀሱ ዘረኞች ይልቅ፣ በይፉ ለተወሰነ ዘር ብቻ እንደቆሙ በግልጽ የሚናገሩትን ማሳመን ወይም የጋራ ጥቅም የሚያመጣም ከሆነ "መስማማት ይቀላል"፡፡ አክራሪ ብሔረተኞች አምነንበታል ብለው የሚያቀርቡት ጥያቄዎች የማንደግፈውም ቢሆንም፣ የሚፈልጉት ግልጽ ስለሆነ፣ ስራውን ለምሁራኖቹ ድርድር ማስረከብ (Elite bargains)፣ አይሆንም ብለው እምቢ ካሉም የመከላከያ ሠራዊት ቀጣይ ተግባር ይሆናል፡፡ ድርብና አስመሳይ አቋም የያዙት ካንገት በላይ ሀገር፣ ዲሞክራሲ፣ አንድነት እያሉ በተግባር የሚደክሙት ለግላቸው ወይም ለአንድ ማኅበረሰብ ብቻ ነው ፡፡

በኢትዮጵያዊነታችን የሁሉንም ማኅበረሰብን መከራውም ሆነ ደስታው እኩል ሊሰማን ሲገባ፣ እነዚህ አስመሳይ አድርባዮች ሀገራችን የሚሉት መሬቱንና ጥቅሙን እንጂ ሕዝቡን አይደለም፡፣ ኦሮሞ፣ አማራ፣ ደቡብ፣ ሰሜን እያሉ ቀንና ማታ ስለ አንድ ብሔር እንጂ የሚጨነቁት ከዛ ውጪ ስላለው ሕዝብ ደንታ የላቸውም፡፡ እነዚህ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች ሕዝብ ሞተ ፣ተፈናቀለ ፣ተጨቆነ ብለው ድምጽ ሲያሰሙ ቆመንለታል ስለሚሉት ማኅበረሰብ እንጂ **"እነሱ"** ስለሚሏቸው ወገኖቻችን፣ ሞታቸው፣ ስደትና ስቃያቸውን እንደ የሰው ፍጡር ስለማይሰማቸው ስማቸውን እንኳን ሲጠሩ አይሰሙም፡፡

እነዚህ የግጭት ነጋዴዎች፣ ፈረንጅ ሀገር የዛሬ አርባ እና ሃምሳ ዓመት መጥተው ከብዙ ቋንቋ ተናጋሪና የተለያየ ዕምነትና ባሕል ካላቸው ሰዎች ጋር፤ ያገሩን ሕግ አክብረው፣ ልጆቻቸውን አሳድገውና ጡረታቸውን አስከብረው በሰላም አብረው እየኖሩ፣ በሀገራችን በሺዎች ዓመታት አብሮ በሰላም ተቀላቅሎ የኖረውን ክቡር ሕዝብ፣ መጤ፣ ሰፋሪ ወራሪ...ወዘተ እያሉ በመከፋፈል እርስ በእርስ እንዲተላለቅ ግፊት ከውጪ ያደርጋሉ፡፡ እነሱ በውጪው ዓለም የሚያጣጥሙትን የሠላም ሕይወት ለራሳቸው እንጂ ሀገር ውስጥ ያለው ወገናችን እንዲኖረው የማይፈልጉ ድርብ አቋም ያላቸው አስመሳዮች ናቸው፡፡

በጣም አድርባይ መሰሪዎች ስለሆኑ የዋሉበት አያመሹም፣ ያመሹበት አያድሩም፡፡ በግለሰብ ደረጃ እንኳን ድርጅት ውስጥ የሚገቡት ወይም እራሳቸው በየሳምንቱ እንደ እንቁላል የሚፈለፍሉት የራሳቸውን በጥላቻ የመረዘ አቋም በመዝራት ለመከፋፈልና በዛ ቀውስ ውስጥ እራሳቸውን ደብቀው ለመጠቀም ስለሆነ፣ አንዳንዴ እየተነቃባቸው ከየድርጅቱና ከየቡድኑ ይባረራሉ ወይ እራሳቸው አፍረው ሾልከው ይወጣሉ፡፡ ከየቦታው ተነቅቶባቸው በተባረሩ ቁጥር ብስጭታቸውና ጥላቻቸውም እየከረረ ስለሚሄድ ይህን እንደዝቋላ በየወቅቱ እየገዘፈ የሚሄድ የቁጭት ስሜት ለማካካስ፣ ማንም "ውጡ ወይም ታገዱ" ብሎ እንዳያባርራቸው የራሳቸውን ሚኒ ድርጅቶች በአንድ ጨረቃ ሌሊት ያቋቁማሉ፡፡ አባላት ለሌለውና ቀፎ ለሆነው ድርጅታቸው ስም እንደ እንቁላል በየሳምንቱ እየፈለፈሉ ያረገዙትን የጥላቻ መርዝ በሀገር እና በሕዝብ ስም እየረጩ ትግልን በማዳከም ኅብረታችንን ይጎዳሉ፡፡

እነዚህ የፖለቲካ ቱጃር ነጋዴዎች፣ ምንም ተንኮል ልቡ ውስጥ የሌለን እና በደል በወገኑ ላይ ያላደረሰን ሠላማዊ ለፍቶ አደር ሕዝብን፣ ከሚጠሏቸው አክራሪዎች ጋር ጨፍልቀው በጅምላ የመስደብና

የማዋረድን መንገድ ሲመርጡ፣ ሳይፈቅዱለት በስሙ የሚሰደቡለትን በሀገር ውስጥ ያለውን ምስኪን ሕዝብ፣ ደም ለጠማቸው የተለያዩ አክራሪ ብሔረተኞች ለብቀላ እንደሚዳርጓቸውና እንደሚያመቿቿቸው ሳይገባቸው ቀርቶ አይደለም፡፡ የሚያቀጣጥሉትም የእርስ በእርስ ግጭት የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶችን ፍላጎት በጓሮ በር እንደሚያሳካም ጠፍቷቸው ሳይሆን በውስጣቸው ያለውን የጥላቻቸው ስሜት ስለሚያበርድላቸው ብቻ ነው፡፡

ሁሉም ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ ዘረኞች ከሕዝብ ይልቅ የሚፈልጉት ስልጣኑንና ንዋዩን ነው፡፡ አቦይ ስብሃት ከሁመራ ሰሊጡን፣ ጃዋር መሃመድ ከአዲስ አበባ ሕንጻውን፣ ልደቱ በጓሮ በር ወደ ወያኔ ሲጠጋ ካሹን፣ መረራ ጉዲና ጠቅላይ ሚኒስቴርነቱን እንጂ ለሚያጭበረብሩለት ሕዝብ ጥቅም አይደለም፡፡

“ቆመንለታል” ብለው ለሚዋሹት መኅበረሰብ፣ መጥቀም ማለት በስሙ አብሮት የሚኖረውን ሕዝብ አጸያፊ ስድብ በመሳደብና በማዋረድ ሊሆን አይገባም፡፡ በእውነት ማኅበረሰቡን ለመርዳት ከፈልጉ መንገዱ ሌላ ነው፡፡ ጠላት አይግዙለት፣ በችግሩ ይድረሱለት፣ ባህሉን ወጉንና እምነቱን ያክብሩለት፣ ሲጠቃ ተደራጅተው ብሶቱን ያሰሙለት፣ ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል ድልድይ ይስሩለት እንጂ፣ እርካሿን ከኪሳቸው ሳንቲም የማያስወጣውን ስድብና ጥላቻን መምረጥ ይጎዳዋል እንጂ አይጠቅመውም፡፡

በየትኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ እንደነዚህ አይነት ግለሰቦች ብዙ ጊዜ የጥላቻቸው መሠረት የሚነሳው ከግል የጥቅም ፍላጎት ይጀምርና፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ለማግኘት ቀስ በቀስ “ፖለቲካዊ ልዩነት” አስመስለው ሊያጭበረብሩ ይሞክራሉ፡፡ ቀጥለውም እራሳቸውን ስር ወደ ሰደደ የዘር ጥላቻ ውስጥ ሳያስቡት ይቀረቀራቃሉ፡፡ ትክክለኛ ተግባራቸውን አደብዝዞ ጥላቻቸውን ለማሰራጨት እንዲረዳቸው ድርጅቶችን እንደ በቆሎ በየሳምቱ እየፈለፈሉ የተለያየ የዳቦ ስም በማውጣት፣ በ12 ወር 24 ድርጅት የመፍጠር ክህሎት እንዳላቸው ታዝበናል፡፡ ታዲያ እንደዚህ አይነት ጉልበት፣ ጊዜና ችሎታ ለጥፋት ተልዕኮ የሚያባክኑት፣ ለሀገርና ወገን ብለው ለበጎ ነገር አለመጠቀማቸው ያስቆጫል፡፡

እንደዚህ አይነት ስብዕና ያላቸው ነጋዴዎች በትግል ሽፋን የግል ጥቅማቸውን ስለሆነ የሚያነፈንፉት ከወያኔ ጀምሮ ያልተጠጉት የጎሳ ድርጅት የለም፡፡ በጥቅም ተጋጭተውና አኩርፈው ሲወጡ በምን ምክንያት ከወያኔነት እንዳፈገፈጉ በግልጽ ሳይናገሩ ነው ባንድ ምሽት ተቃዋሚ ሆነናል ነው የሚሉት፡፡ ከወያኔ የተባረሩበትን ምክንያት እነሱም የሚደብቁላቸውና እኛም የማናውቅ ይመስላቸዋል፡፡ በአዲሱም የአቢይ መንግስት ዘመንም፣ ትኩረት መሳብያ ትናንሽ ሱቅ በደረቴ ድርጅቶች በ24 ሰዓት ቀፍቅፈው በየስብሰባው ቀልብ ስበው እውቅና ለማግኘትና ለመሾም ሞክረው ንቀዋቸው ፊት ሲነሷቸው፣ ያንን ሃፍረትና ብስጭት ለማካካስ በተቃዋሚ ስም ሆድ አደሮችን አሰባስበው ተቃውሞ ሳይሆን ጥላቻን ባደባባይ ያሰራጫሉ፡፡

ተስፋ የሚያደርጉት ግን የመንግሥትን ቀልብ በዚህ አይነት ስበው “ኑ በቃ ይቅር ለቤታችሁ፣ አይዟችሁ ስልጣንም ይሁን ገንዘብ ታገኛላችሁ” የሚል ጥሪ እየጠበቁ በተስፋ ቅዠት ሳይተኙ እየቋመጡ ያድራሉ፡፡ ምኞታቸው ሳይሳካ ሲቀር ጥላቻቸውም ስለሚከር፣ ይበልጥ ገዝፎ ለመታየና ያሰቡበት ባቋራጭ ለመድረስ፣ የተለያዩ “የተቃዋሚ” መደራደርያ ድርጅቶችን ከፋብሪካ በፈጠነ መልኩ ማምረቱን ያጧጡፉታል፡፡ የተቃዋሚዎች እራስ፣ የሽንጎዎች ጠቅላይ፣ የአሰባባሳቢዎች ግንባር፣ የጠቅላዮች ወራሽ፣ የበላዮች በላይ፣ የጭቃ ሹም፣ የምስለኔ ፓርቲ ምናምን ...ወዘተ እያሉ የሀገራችንን ስሞች ጨርሰው፣ በቅርቡ በቻይንኛ ሳይጀምሩ አይቀርም እየተባለ ይወራል፡፡ ለስልጣን ማበድ ማላት ከዚህ በላይ ምንድነው?

ከአንዳንዶቹ ጋር እንኳን “አብሮ መታገል ለልፊያም” የማይመቹም ናቸው፡፡ ዲሞክራሲ ስሙን እንጂ ተግባሩ ምን እንደሆነ እንዳይገባቸው የተደገመባቸው እስከሚመስሉ፣ ስለየተሻለ አስተዳደር፣ የመንግስት ለውጥ፣ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ...ወዘተ አምርረው ሲቃወሙ የሚሰሙት፣ እራሳቸው ያውም በሰለጠነው ዓለም ውስጥ ቀንድ እስከሚያበቅሉ ለዓመታት በያዝዋቸው ትናንሽ የሃላፊነት ቦታዎች፣ እዛው የበቀሉ ወይም የተተከሉ እስከሚመስሉ ድርቅ ብለው ሲቆዩ፣ ምርጫ፣ ኦዲት ሪፖርት፣ ጠቅላላ ስብሰባ የሚባሉት ተሸረው ዘላለማዊ ንግስናን እንደ እንደተካኑ፣ የማኅበርን ማህተም እንደተክሊል በየኪሳቸው በመያዝ፣

አስር ሰው የተሰበሰበበት ቦታ እንደ ሊቀመንበር መዝጊያና መክፈቻ ዲስኩር ለማድረግ ሁሌ ሲቃጣቸው የሚታዩ ብዙ "ትንንሽ ንጉሦችን" ማየት ማስደነቁ ቀርቷል፡፡ እነሱም ይሉኝታና ማፈር የሚባለውን ጣጣ አሽቀንጥረው ከጣሉት ዓመታት ሆንዋቸዋል፡፡ በተለይ አንድ መከላከያ ብሄር ከኋላቸው "ያንተው ነን" ብለው የነጠላይቷን ጫፍ ከያዙ በኋላ "እከክልኝና ልከክልህ" ስለሆነ ገልመጥ አንኳን አይደረጉም፡፡

ፍላጎታቸውን በግልጽ ማካሄድ ስለማይደፍሩ፣ የመረጡት መንገድ ያልሆኑትን መስለው ድርብ አቋም (double standards) በመያዝ "የአንድነት ወይም የኛነት" ብለው ከመረጧቸው ድርብ ድርጅት እቅፍ ውስጥ ሆነው፣ አንድ እግራቸውን አንድነት፣ ሌላውን የብሔር ድርጅት ገበቴ ውስጥ ዘፍዝፈው ትግሉን እያንቦጫረቁ እንዲጫወቱ ወቅቱ የተመቻቸላቸው ይመስላል፡፡ እንደነዚህ አይነት ሀገር በቀል ሰዎች በየቦታው እራሳቸው ሠላም አጥተው መሰሎቻቸውን በማሰባሰብና አብረው በጥላቻ በማበድ (Mass Psychosis) በጋራ የሚሰማቸውን አደገኛ የጥላቻና የበቀል ስሜትን ወደ ሕዝባችን ውስጥ አሰርጸው ለማስፋፋት የሚጥሩትን በያለንበት ተው! ኅብረትንና ትግሉን ይጎዳል ብንላቸው ይበጃል፡፡

ባጠቃላይ አክራሪዎቹም ሆኑ የቀውስ ነጋዴዎቹ፣ በኢትዮጵያዊነት ተሰባስበን በኅብረት እንድንቆም፣ ተባብረን እንድንቃወምም ሆነ እንድንደግፍ፣ ባጠቃላይ፣ ከብሔረተኞቹ ፍላጎት ውጪ እንድንገናኝ ስለማይፈልጉ የራሳችንን አማራጭ መፈለግ ወቅቱ አሁን ይመስላል፡፡ እንግዲህ መክረን ዘክረን ጠብቀን ሰሚ ከጠፋ፣ ብሔራችንም ሆነ ዜግነታችን ኢትዮጵያ ናት የምንል፣ አክራሪዎቹን ጭምር ነፃ ለማውጣት፣ በኢትዮጵያዊ የአንድነት መንፈስ ለሁሉም ሕዝባችን እኩል ማገልገል የምንፈልግ ሁሉ የራሳችንን አማራጭ በመፈለግ፣ በየማእዘኑ በቆሙ አክራሪ ብሔርተኞች የተዳከመውን የመሃል ኅብረ-ብሔራዊ እንቅስቃሴ ጠወለገ እንጂ ስላልደረቀ፣ በኢትዮጵያዊነት የሀገር ፍቅር፣ በመከባበርና በመረዳዳት ተደጋግፈን እየተቻቻልን፣ **መላው ኢትዮጵያ፣ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ናት** በሚል መርኅ እንደገና በመሰባሰብና በመቀናጀት የአንድነትን መንፈስን ለማጠናከር የምንችልበትን መንገድ እናስብ፡፡

በተረፈ ባለፉት ጽሁፎቼ ጥቂት አስተያየት ሰጪዎች በኢሜልና  በመልዕክት መቀበያ፣ "ያቀረብከው ዘገባ ስለ እከሌ ነው፣ ስለ እዚህ መኅበረሰብ ነው፣ ስለዛ የፖለቲካ ድርጅት ነው" ላላችሁና፣ ለወደፊትም ለምትሉ፣ ለአስተያየታችሁና ጥቆማችሁ ምስጋናዬን በማክበር ከወዲሁ በማስቀደም፣ ስለየምታውቁት ነገር ከራሳችሁ በላይ ምስክር የለምና>>>>>>› **Who the shoe fits, let them wear it!**

**ብስራት ኢብሳ (ሆላንድ)**

**በእኩልነት ላይ የተመሠረተች አንድ ኢትዮጵያ፡፡** **tebaber@gmail.com**

**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ፣ እኛም እንተባበረው፡፡**

**የመጀመርያዎቹ ቁጥር አንድ እና ቁጥር ሁለትን ላላገኛችሁ ከዚህ በታች ያሉትን መስፈንጥርያዎች ይጫኑ!**

http://almariam.com/wp-content/uploads/2016/11/Zemene-Mederegnanet-Bisrat-Ibssa.pdf

http://almariam.com/2018/09/26/%e1%8b%98%e1%88%98%e1%8a%90-%e1%88%98%e1%8a%95%e1%8b%b0%e1%88%ad%e1%89%b0%e1%8a%9b-%e1%8a%ad%e1%8d%8d%e1%88%8d-%e1%88%81%e1%88%88%e1%89%b5-22-9-2018/

http://www.ethiopanorama.com/wp-content/uploads/2020/01/%E1%8B%A8%E1%8B%98%E1%88%98%E1%8A%90-%E1%88%98%E1%8A%95%E1%8B%B0%E1%88%AD%E1%89%B0%E1%8A%9B-%E1%8B%A8%E1%88%98%E1%8C%A8%E1%88%A8%E1%88%BB%E1%8B%8D-%E1%88%9D%E1%8B%95%E1%88%AB%E1%8D%8D-%E1%89%81%E1%8C%A5%E1%88%AD-3-1.pdf